# የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ የክፍያ ካርድ አገልግሎት ውል

ይህ የክፍያ ካርድ አገልግሎት **ውል ዛሬ**............ቀን ......ዓ.ም. በ .........·.........·.................. ከዚህ በኃላ **"ደንበኛ"** እየተባሉ በሚጠሩት፤ እና **በንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ** ...............**ቅርንጫፍና ከዚህ በኋላ "ባንክ"** የተባለ በሚጠራው መካከል ተፈርሟል::

## 1. የውሉ ዓላማ

1.1. ባንኩ የደንበኞችን መብትና ክብር በጠበቀ ሁኔታ ቀልጣፋ የክፍያ ካርድ አገልግሎት ለማቅረብ ዝግጅቱን አጠናቆ ወደ ሥራ የገባ በመሆኑ፤

1.2. ደንበኛውም ዘመናዊና ቀልጣፋ የክፍያ ካርድ አገልግሎት ከባንኩ ለማግኘት በመፈለጉ ሁለቱም ወገኖች ወደውና ፈቅደው ይህንን የክፍያ ካርድ አገልግሎት ውል ተፈራርመዋል::

## 2. ትርጓሜ

በዚህ የክፍያ ካርድ አገልግሎት ውል መሠረት: -

2.1. **"የባንክ ሂሣብ"** ማለት ደንበኛው የከፈታቸውና የሚጠቀምባቸው እንዲሁም ለዚሁ ካርድ አገልግሎት ወደፊት የሚከፍታቸው ማንኛውም የባንክ ሂሣቦች ማለት ነው::

2.2. **"ካርድ"** ማለት በደንበኛው ጥያቄ መሠረት በስሙ ተዘጋጅቶ በንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የተሰጠ የክፍያ ካርድ ማለት ነው::

2.3. **"ባለ ካርድ"** ማለት የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የክፍያ ካርድ በስሙ ታትሞለት አገልግሎት እንዲያገኝ የተፈቀደለት እና ይህንን ውል የተቀበለ ደንበኛ ማለት ነው::

2.4. **"የማንነት ማለያ ቁጥር"** ማለት ባለካርዱ በክፍያ ካርድ አገልግሎት ማሽኖች ለማስተናገድ የሚያስችለው የባለቤትነት ማረጋገጫ ቁጥር ነው::

2.5. **"የልውውጥ ትዕዛዝ"** ማለት በባለካርዱ የተሰጠ የክፍያ ትዕዛዝ ማለት ነው::

2.6. **"የጥምር ሂሣብ/ ተጣማሪ ተጠቃሚ"** ማለት ደንበኛው በዚህ ውል መሠረት የሚያገኘውን አገልግሎት በጋራ የሚጠቀም ደንበኛ ማለት ነው::

2.7. በዚህ ውል ወስጥ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር: -

2.6.1. **"ተርሚናል"** ማለት የልውውጥ ትዕዛዞችን የሚያስተናግድ አውቶሜትድ የክፍያ ማስጫ ማሽን ማለት ነው::

2.6.2. በወንድ ጾታ የተገለጹት ሁሉ ለሴትም ጾታ በእኩልነት ያገለግላል::

2.6.3. በነጠላ ቁጥር የተገለጹት ለብዙ ቁጥር እንዲሁም በብዙ ቁጥር የተገለጹት ለነጠላ ቁጥር ያገለግላል::

Approved by the Board of Directors On Sep 401.2014

## 3. የደንበኛው መብትና ግዴታ

3.1. በክፍያ ካርድ አገልግሎት ለመጠቀም መፈለጉን የሚገልጽ በባንኩ በተዘጋጀ የሃገር ወስጥ ኤሌክትሮኒክ የክፍያ ካርድ አገልግሎት መጠየቂያ ማመልከቻ ቅጽ ሞሉ አድራሻውንና ማንነቱን የሚገልጽ መረጃዎችን በመሙላት ፈርሞ ማቅረብ፤ ተጣማሪ ተጠቃሚ ካለውም ይህንኑ ከነአድራሻው በማመልከቻው ላይ ጨምሮ መግለጽ፤

3.2. ባንኩም በማመልከቻው መሠረት ተገቢውን ማስፈርት መሟላቱን አረጋግጦ የክፍያ ካርድ ሲያዘጋጅ የክፍያ ካርዱንና የማንነት ማለያ ቁጥሩን ከባንኩ መረከብ::

3.3. ከባንኩ በተረከበው የክፍያ ካርድ ባንኩ በሚያወጣው የክፍያ ካርድ አጠቃቀም መመሪያ መሠረት በአግባቡ ማጠቀም፤ እንዲሁም በክፍያ ትዕዛዝ ወጪ ላደረገውና ለተጠቀመበት የአገልግሎት ክፍያ ከሂሣቡ ተቀናሽ እንዲሆን መፍቀድ::

3.4. በክፍያ አገልግሎት ማስጫ ማሽኑ የሚደረግ ወጪን በተማከተ በአንድ ቀን ከተፈቀደው የገንዘብ ማጠን በላይ ወጪ አለማድረግ::

3.5. እንዲሁም በባንክ ሂሳብ ካለው ገንዘብ በላይ ወጪ (overdrawal) አለማድረግ፤

3.6. ከባንኩ የተረከበውን የክፍያ ካርድ እና የማንነት ማለያ ቁጥርን በከፍተኛ ጥንቃቄ እና ጥበቃ መያዝ:: የክፍያ ካርድ እና የማንነት ማለያ ቁጥርን ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሣልፎ አለማስጠት::

3.7. የጥምር ሒሣብ አገልግሎት ተጠቃሚ ደንበኛ ከተጣማሪው ካርድ ተጠቃሚ በስተቀር ለሌላ ሦስተኛ ወገን የክፍያ ካርድ እና የማንነት ማለያ ቁጥርን አሣልፎ አለማስጠት::

3.8. የክፍያ ካርዱ ከጠፋ፤ ከተሰረቀ፤ ወይም የማንነት ማለያ ቁጥሩ ባልተፈቀደለት ሰው ወይም አካል መግባቱን እንዳወቀ ወዲያውኑ ለባንኩ ማሣወቅ፤ ማሣወቁ የተደረገው በቃል ወይም በስልክ የተላለፈ መልዕክት ከሆነ ወዲያውኑ በጽሁፍ ለባንኩ በአካል በመቅረብ ማረጋገጥ::

3.9. የክፍያ ካርዱ ለክፍያ አገልግሎት ብቻ የሚውል በመሆኑ ለክሬዲት ካርድ፤ ለቼክ ማስከበሪያ፤ ወይም ለልዩ ልዩ ዕዳ ማስከበሪያ ወይም መያዣ የማያገለግል ስለሆነ ለእነዚሁ ተግባራት አለማጠቀም::

## 4. የባንኩ መብትና ግዴታ

4.1. የክፍያ ካርድ አገልግሎት ለማግኘት ለሚመጣ ደንበኛ የሃገር ወስጥ ኤልክትሮኒክ የክፍያ ካርድ ማመልከቻ ቅጽ በማዘጋጀት እንዲሞላ ማድረግ፤ እንዲሁም ደንበኛው አስፈላጊውን ማስፈርት ማሟላቱን በማረጋገጥ የክፍያ ካርድ እና የማንነት ማለያ ቁጥር ማስጠት::

4.2. ደንበኛው ተጨማሪ የክፍያ ካርድ ከጠየቀ ወይም ከሂሣቡ ሌላ ተጣማሪ የካርድ ተጠቃሚ እንዲገለገል ከፈቀደ አስፈላጊውን ማስፈርት

እንዲያሟሉ በማድረግ ተገቢውን አገልግሎት ማስጠት፡፡

4.3. የክፍያ ማሽን በማዘጋጀት በአመቺ ስፍራ ለደንበኞች አገልግሎት ማስጠት፡፡ ተገቢውን አገልግሎት ለማስጠት ብቁ ሠራተኞችን መመደብ፡፡

4.4. ለደንበኛው ተገቢውን አገልግሎት በማስጠት ደንበኛው በክፍያ ትዕዛዝ ወጪ ያደረገውን ከደንበኛው የባንክ ሂሣብ መቀነስ፡፡ እንዲሁም ደንበኛው ለተጠቀመበት የአገልግሎት ክፍያ (Service charge) ተቀናሽ ማድረግ፡፡ በክፍያ አገልግሎት መስጫ ማሽኑ ላይ የደንበኛውን የመጨረሻ ሂሣብ መጠን (balance) መግለጽ፤ የሂሣብ መግለጫ ማስጠት፡፡

## 5. የካርድ እና የማንነት መለያ ቁጥር

5.1. አንድ ካርድ ከባለ ካርዱ በስተቀር ለሌላ ሊተላለፍ አይችልም፡

5.2. የክፍያ ካርድ ባለቤትነት የባንኩ በመሆኑ አገልግሎቱ በተቋረጠ ጊዜ ካርዱ ለባንኩ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

## 6. የደንበኛው የባንክ ሂሣብ

6.1. ደንበኛው ለክፍያ ካርድ አገልግሎት የሚውል የባንክ ሂሣብ ወይም ለተጣማሪ የካርድ ተጣቃሚ አገልግሎት የሚውል የጋራ ሂሣብ በሃገር ወስጥ ኤሌክትሮኒክ የክፍያ ማመልከቻ ቅጽ ላይ በተገለጸው መሠረት ይሆናል፡፡

6.2. በዚህ ውል ከተገለጹት በተጨማሪ የደንበኞችን ሂሣብ የሚመለከቱ የባንኩ መመሪያዎች የጸኑ ይሆናሉ፡፡

## 7. ምትክ ካርድ ስለማግኘት

7.1. ደንበኛው የክፍያ ካርዱ ቢጠፋበት፤ ቢሰረቅ፤ ወይም በሌላ ሶስተኛ ሰው መለያ ቁጥሩ ቢታወቅ ወይም የክፍያ ካርዱን ማስቀየር ቢፈልግ ለባንኩ በማሣወቅ ምትክ ካርድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

7.2. ባንኩ የደንበኛው ጥያቄ በደረሰው አንድ ሣምንት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ምትክ ካርድ አዘጋጅቶ ደንበኛው በሚገለገልበት ቅርንጫፍ በኩል እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡

## 8. የክፍያ ካርድ አገልግሎትን ስለማስረዝ

8.1. ደንበኛው በማንኛውም ጊዜ የክፍያ ካርዱን ለባንኩ በመመለስ የአገልግሎት ተጠቃሚነቱን ለማቋረጥ ይችላል፡፡

8.2. ባንኩ የደንበኛውን የካርድ አገልግሎት ማቋረጥ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ምክንያቱን ለደንበኛው መግለጽ ሣያስፈልገው የካርድ አገልግሎት ለማቋረጥ ይችላል፡፡

8.3. ደንበኛው የክፍያ ካርድ አገልግሎቱ መቋረጡ ከባንኩ እንደተገለጸለት በካርዱ ማጠቀምም ሆነ ለማጠቀም መሞከር አይችልም፡ ካርዱን ለባንኩ ወዲያውኑ መመለስ አለበት፡፡

## 9. የአገልግሎት ክፍያ

ባንኩ ለደንበኛው ለሚሰጠው የካርድ ክፍያ አገልግሎት ክፍያ (Service charge) ባንኩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ባንኩም ይህንን የአገልግሎት ክፍያ ከደንበኛው ሂሣብ የመቀነስ መብት አለው፡

## 10. ኃላፊነት

10.1. ደንበኛው በካርድ ለሚፈጸሙት የክፍያ ትዕዛዞች ሁሉ ሙሉ ኃላፊነት አለበት፡፡

10.2. በመሆኑም ካርዱ በመጥፋቱ፤ በመሰረቁ ወይም በማናቸውም ምክንያት ካርዱ እና መለያ ቁጥሩ በማይመለከታቸው ሦስተኛ ወገኖች እጅ በመግባት ለሚደረጉ ክፍያዎች ባንኩ ምንም ኃላፊነት የለበትም፡

## 11. ማሻሻያ

11.1. ይህ የካርድ ክፍያ አገልግሎት ውል ባንኩ በማንኛውም ጊዜ ለደንበኛው በማስታወቅ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

11.2. ማሻሻያው ተግባራዊ የሚሆነው ባንኩ የማሻሻያው ማስታወቂያ በጽሁፍ ለደንበኛው ካደረሰበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

## 12. ተፈጻሚ ሕጎች

ይህ የካርድ ክፍያ አገልግሎት ውል በንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የካርድ ክፍያ አገልግሎት መመሪያና ደንብ እንዲሁም አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሚተረጎምና የሚመራ ይሆናል፡፡

ይህ የካርድ ክፍያ አገልግሎት ውል ዛሬ ................ ቀን......ዓ.ም ምስክሮች በተገኙበት በደንበኛው እና በባንኩ የሥራ ኃላፊ ተፈርሟል፡፡

**የአንደኛ ደንበኛ (አመልካች) ስምና ፊርማ**

ስም........................ ....... ፊርማ..................................

ቀን........ ...........................

**የሁለተኛ ደንበኛ (አመልካች) ስምና ፊርማ**

ስም...................................ፊርማ..................................

ቀን ...........................

**የባንኩ የሥራ ኃላፊ ስምና ፊርማ**

ስም..............................የሥራ ኃላፊነት ........................

ፊርማ ................................ቀን ........................ ...........

የቅርንጫፉ ማህተም ____________________

**ምስክሮች**

**ስም** ............................ **ስም** ............................

**ፊርማ** ............................ **ፊርማ** ............................

**ቀን** ...... ........................ **ቀን**...... ......................

# የንብ ካርድ ማማልከቻ ቅጽ

# NIB Card Application Form

## ዋና አመልካች
## Principal Applicant

ሙሉ ሥም ከነአያት ______________________________

Full Name including Grand Father Name ______________________________

ማዕረግ ____________________

Desigination ________________

ጾታ፡ ወንድ ☐ ሴት ☐

Gender: Male Female

አድራሻ: ከተማ______________ ክፍለ ከተማ __________ ወረዳ/ቀበሌ ________ የቤት ቁጥር____________

Address: City/Town Sub City Woreda/kebele House No.

የመኖሪያ ቤት ስልክ ቁጥር ______________ ሞባይል ______________ የቢሮ ስልክ ቁጥር ______________

Home Tel. No. Mobile Office Tel. No.

እርስዎ ከሚያንቀሳቅሱት የባንክ ሂሳብ ጋር የሚገናኝ ተጨማሪ ካርድ ለቅርብ የቤተሰብዎ አባል እንዲሰጠው የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ ቀጥሎ ከተመለከቱት ሳጥኖች ውስጥ ያስፈልገኛል በሚለው ምርጫ ትይዩ በሚገኘው ሳጥን ውስጥ ምልክት ያድርጉና ከዚህ በታች የተመለከተውን ቅጽ ተጨማሪ ካርድ በሚያስፈልገው አመልካች ይሞላ፡፡

ያስፈልገኛል ☐ አያስፈልገኝም ☐

Please indicate if you need a secondary card for your immediate family members which will be linked to your account ☐ Yes ☐ No

## ተጨማሪ አመልካች

## Secondary Applicant

ሙሉ ሥም ከነአያት ______________________________

Full Name including Grand Father Name ______________________________

ማዕረግ ____________________

Desigination ________________

ጾታ፤ ወንድ ☐ ሴት ☐

Gender Male Female

አድራሻ: ከተማ______________ ክፍለ ከተማ __________ ወረዳ/ቀበሌ ________ የቤት ቁጥር____________

Address: City/Town Sub City Woreda/kebele House No.

የመኖሪያ ቤት ሥልክ ቁ. ______________ የቢሮ ስልክ ቁ. ______________ የሞባይል ሥልክ ቁ.______________

Home Tel. Office Tel. Mobile

## የባንክ ሂሳብ ዝርዝር
## Account Details

ለክፍያ ካርድዎ የመረጡት የባንክ ሂሳብ፡ የቁጠባ ሂሳብ ☐ የልዩ ቁጠባ ሂሳብ ☐ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ☐ የሂሳብ ቁጥር

Preferred Account for your Card: Savings Special Saving Current Acct.No. ______________

ቅርንጫፍ

Branch______________________

ከክፍያ ካርድዎ ጋር እንዲገናኝልዎት የሚፈልጉት ተጨማሪ የባንክ ሂሣብ ካለ

Indicate another Account to be linked to your debit card (If required)

የባንክ ሂሳብ ዓይነት የሂሳብ ቁጥር ቅርንጫፍ ____________

Type of account ______________________Account No.__________ Branch ____________

ባለካርዱ ተጨማሪ አመልካች በሂሳባቸው እንዲጠቀም ጠይቀው የተፈቀደላቸው እንደሆነ ማንኛውም ዓይነት በሌለኛው ወገን የሚደረግ የካርድ ክፍያን እንደሚቀበሉ ተስማምተዋል፡፡

In the case of joint card application we acknowledge that transactions made by one of us using the card shall be accepted by the other.

______________________________ ______________________________

የዋናው አመልካች ፊርማ | የሁለተኛው ካርድ አመልካች ፊርማ(ካለ)

Signature of Principal Applicant | Signature of Secondary Applicant (If any)

ቀን | ቀን

Date ______________________ | Date ______________________

---

**ለቢሮ አገልግሎት ብቻ**

**For Office use only**

**Branch**

Balance of primary A/C on the date of Application ______________________

Branch Manager Comment/Decision ______________________________

Date ______________________ Signature ______________________

Approved by the
Board of Directors
On Sept 01, 2014